# የዓለም ባንክ “ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ” ሪፖርት

**ቶሎሳ ኡርጌሳ** 07/28/14

Utolosa@yahoo.com

የዓለም ባንክ ሀገራችንን በተመለከተ ከነባራዊው ዕውነታ ጋር የሚጣረስ አንድ ሪፖርት ሰሞኑን አውጥቷል። የሪፖርቱ ጭብጥ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ፣ ኢትዮጵያ በተለያዩ ዘርፎች በተለይም በአገልግሎት ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለውጭ ዜጎች ዕገዳዎች እንዳላትና በዚህም ሳቢያ የወጪ ንግድ መዳከሙን የሚያትት ነው። ለውጭ ዜጎች ተከለከሉ ካላቸው ዘርፎች ውስጥ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ የፋይናንስ አገልግሎቶች፣ ሚዲያ፣ የችርቻሮ ንግድ እና ትራንስፖርት እንደሚገኙባቸውም ገልጿል።

ታዲያ ሪፖርቱን ተከትሎ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ከመሰንበቻው ከሲኤንቢሲ (CNBC) ቴሌቪዥን ጋር ቃለ-ምልልስ አካሂደው ነበር። በቃለ-ምልልሳቸው ላይም የዓለም ባንክ ያወጣው ሪፖርት በሀገራችን ውስጥ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ትውውቅ የሌለው መሆኑን ተናግረዋል። የዓለም ባንክ ኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ስራ እንዴት እንደሚከናወን ያለው እሳቤ የተሳሳተ መሆኑንም አስረድተዋል።

ሀገራቸው አሁን ባለችበት የመጀመሪያ የዕድገት ምዕራፍ ላይ ባንኩ የዘረዘራቸውን የአገልግሎት ዘርፎች ለውጭ ባለሃብቶች ክፍት ማድረግ እንደማትችል፣ ነገር ግን ሀገራዊ የልማት ተዋንያኖችና ዘርፎች አቅማቸው ሲጎለብት ዘርፎቹን ለባለሃብቶቹ ክፍት ይደረጋሉ ብለዋል–ኢትዮጵያ በዚያን ወቅት ይበልጥ ተወዳዳሪ መሆን ስለምትፈልግ። የኒዮ-ሊበራል ስርዓት ቀያሾቹ ማርጋሬት ታቸርና ሮናልድ ሬጋን ርዕዮቱን ስላወጁ ብቻ፣ ኢትዮጵያ አሁን በምትገኝበት ጅምር የዕድገት ደረጃ ትቀበለዋለች ማለት አይደለም ሲሉም የባንኩን የተደበቀ ፍላጎት ገልፀዋል። እንደ ማንኛውም ጀማሪ ምጣኔ ሃብት ባለባቸው ሀገራት ውስጥ ሁሉ፣ ኢትዮጵያም ውስጥ በግል ባለሃብቱ ሊሸፈን የማይችል

ትልቅ የገበያ ክፍተት መኖሩን የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በዚህም ሳቢያ በሀገሪቱ ውስጥ የመንግስት "ጠንካራ እጆች" መረጋገጥ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

እርግጥም ሀገራችን ለዕድገቱ ገና ጀማሪ በመሆኗና የሀገራችንም ባለሃብት አቅሙ ይህን ያህል ያልጎለበተ በመሆኑ መንግስት የባለ ሃብቱን ሚና በማይጋፋ መልኩ በተመረጠ መልኩ ጣልቃ መግባት ይኖርበታል–በየትኛውም ታዳጊ ምጣኔ-ሃብት እንደሚደረገው። ሌላው ቀርቶ እነ አሜሪካና እንግሊዝ ከዛሬ ሁለት መቶ ዓመታት በፊት አቅማቸው በሚገባ እስከሚፈረጥም ድረስ ይህንኑ መንግስት በምጣኔ-ሃብቱ ውስጥ ጣልቃ የሚገባበትን አካሄድ ሲከተሉ እንደነበር አይዘነጋም።

ዳሩ ግን የኒዮ-ሊበራሎች ተቋም የሆነው የዓለም ባንክ እንደምን ይህን የታሪክ ዳራ ሊዘነጋው እንደቻለ ለማንም ግልፅ አይደለም። ለነገሩ እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ትልቁ ጉዳይ 'ዕውን አሜሪካና እንግሊዝ በዚያ በኢኮኖሚ ጮርቃ ጊዜያቸው ሁሉንም ነገር ለባለ ሃብቱና ለገበያው መተው አለባችሁ' ቢባሉ ይቀበሉት ይሆን? የሚለው ጉዳይ ነው። ታዲያ ጥያቄውን ለመመለስ ወደ ዕውነታው ጓዳ ስንመለስ እነዚህ የዛሬዎቹ የፈረጠመ ኢኮኖሚ ባለቤቶች ውንጥያቄ እንኳንስ ሊፈፅሙት ቀርቶ ሊሰሙትም የሚፈልጉት አለመሆናቸው ነው። ምክንያቱም በማደግ ላይ ባለ ኢኮኖሚ ውስጥ የመንግስት ሚና የቀጨጨ መሆን እንደሌለበት በሚገባ ስለሚገነዘቡት ነው።

እናም የዓለም ባንክ "የኒዮ-ሊበራሊዝምን ቀበቶ አሁኑኑ በደንብ ካልታጠቃችሁ የወጪ ንግዳችሁ ይዳከማል" የሚለው የገደምዳሜ ሪፖርት አግባብ የሌለው ብቻ ሳይሆን "ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ" በመሆኑ ተቀባይነቱ ቦታ ሊኖረው አይችልም። እርግጥ ማንም የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው የሆነው የዓለም ባንክ እንዲህ ዓይነቱን ጊዜውን ያልጠበቀ ሪፖርት ማውጣቱ ግልፅ ይመስለኛል። ይኸውም ባንኩ ከሚከተለው የርዕዮተ-ዓለም በመነሳት በግድ የኒዮ-ሊበራሊዝምን ጥብቆ እንድንለብስ እያስገደደን መሆኑ ነው። ይሁንና ያለጊዜው የተዘጋጀና በልካችን ያልተሰፋው ጥብቆ ሊሰፋን አሊያም ሊጠበን እንደሚችል ባንኩ ሊገነዘበው የፈለገ አይመስልም። በተለይም የወጪ ንግዱ ዕድገት እንዲስፋፋ መንግስት ብር ከዶላርና ከሌሎች የመገበያያዎች ገንዘቦች ጋር ያለው የምንዛሬ መጠን እንዲቀንስ ያቀረበው አማራጭ ሀገራችን ውስጥ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አብሮ ስለማይሄድ ፈፅሞ ቅቡል ሊሆን አይችልም።

እንደሚታወቀው በእስካሁኑ የኢኮኖሚ ዕድገት የመንግስት “ጠንካራ እጆች” የማይተካ ሚና ተጫውተዋል። በምሳሌነት የዛሬ ሶስት ዓመት ገደማ በሀገራችን ውስጥ ተከስቶ የነበረውን የዋጋ ግሽበትን በመቆጣጠር ረገድ መንግስት ተጠቃሽ ሊባል የሚችል ተግባርን አከናውኗል። እ.ኤ.አ በ2011 እና በ2012 በቅደም ተከተላቸው 39 ነጥብ ሁለት እና 15 ነጥብ ስድስት በመቶ የነበረውን የዋጋ ግሽበት እ.ኤ.አ በ2013 ወደ አንድ አሃዝ (ማለትም ወደ 7 ነጥብ ዘጠኝ በመቶ) ዝቅ እንዲል አድርጓል። ይህን ዕውነታ ደግሞ የዓለም ባንክ ጠንቅቆ ያውቀዋል። እናም የብር የምንዛሬ መጠንን መቀየር (ለምሳሌ አሁን ከዶላር ጋር ካለው የ20 ብር ምጣኔ ወደ 30 ብር ከፍ ማድረግ) መንግስት በማረጋጋት ላይ የሚገኘውን የዋጋ ግሽበት ቀደም ወዳሉት ጊዜያት የሚመልሰን ይሆናል። ምክንያቱም የብር የመግዛት አቅም ያንስና ከውጭ የምናስገባቸውን ምርቶች በከፍተኛ ዋጋ እንድናስገባ እንገደዳለን። ይህም የተረጋጋውን ኢኮኖሚ ወዳልተፈለገ ሌላ አስቸጋሪ አቅጣጫ እንደሚመራው የታወቀ ነው። ህዳሴያችንን በቅርበት ዕውን ለማድረግ ያሰብነውን ትልምም እንዳናሳካ የራሱን አሉታዊ ጫና መፍጠሩ አይቀርም። ስለሆነም የዓለም ባንክ ሪፖርት የምዕራቡን ርዕዮት በማስተጋባትና ተጠቃሚነቱን ከማመቻቸት በስተቀር፣ ለሀገራችን የሚሰጠው ይህ ነው የሚባል ፋይዳ ያለው አይመስለኝም።

ምንም እንኳን የዓለም ባንክና ሌሎች የኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮት አቀንቃኞች ታዳጊ ሀገራት ከእነርሱ ቀኖና ውጪ የሚያድጉ ባይመስላቸውም፤ ያለ ኒዮ-ሊበራሊዝም ማደግ እንደሚቻል እንደ ቻይና ካሉ “የኤስያ ነብሮች” (Asian Tigers) እንዲሁም ኢትዮጵያን ከመሳሰሉ “የአፍሪካ ነብሮች” (African Tigers) ተጨባጭ ምጣኔ-ሃብታዊ እመርታ መገንዘብ ያለባቸው ይመስለኛል። እርግጥ የዓለም ባንክ “የነብሮቹን” ሽምጥ ኢኮኖሚያዊ ግልቢያ በሚገባ ከማወቅ ባለፈ ራሱም ጭምር በየጊዜው ጥናት እያካሄደ ምስክርነት የሚሰጥበት ጉዳይ ሆኖ ሳለ፤ “ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ” ሪፖርትን ደስ ባለው ወቅት እያተመ በማውጣት ለምን አሉታዊ ሚና ለመጫወት እንደሚፈልግ የሚያስገርም ነው። ያም ሆነ ይህ ግን ዓለም ባንክን ጨምሮ ማንኛውም የኒዮ-ሊበራል አቀንቃኝ ተቋም ታዳጊ ሀገራት በራሳቸው ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ተመርተው በውጤታማ የለውጥ ጎዳና ሲተሙ ለምን ይህን መሰሉን ሪፖርት “ጀባ” እንደሚሉ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው—“ሀገራት ለምን ከእኛ ‘ጣፋጭ’ ፖለቲካዊ-ኢኮኖሚ ፍልስፍና ውጪ ያድጋሉ?!” የሚል አጉል አስተሳሰብ።

ጻሩ ግን ኒዮ-ሊበራሊዝም በአፍሪካ ውስጥም ይሁን በራሳቸው ሀገር የፈጠረው ተጨባጭ ምስቅልቅል እነርሱ እንደሚያሞካሹት 'የችግሮች ሁሉ መፍትሔና ጣፋጭ' የሆነ አይመስለኝም። የተገላቢጦሽ እንጂ። ነገሩ እንዲህ ነው።... እንደሚታወቀው ካለፉት 40 ዓመታት በፊት አፍሪካ የኒዮ-ሊበራሊዝምን ፖለቲካዊና ምጣኔ ሃብታዊ ርዕዩተ-ዓለም ሳታላምጥ እንድትውጥ በመደረጓ፣ የርዕዩቱን ጣጣዎች ተሸክማና የላሸቀ ኢኮኖሚ ባለቤት ሆና እንደ ዔሊ እንድታዘግም ተገድዳ ነበር–እምቅ የተፈጥሮ ሃብት እያላት በድህነቷ አረንቋ ውስጥ መዳከሯና ይህን ተከትሎም በውስጧ የተፈጠሩት የእርስ በርስ ጦርነቶች፣ ከባቢያዊ ግጭቶችና መሰል ተግዳሮቶቿ ህያው ምስክር ናቸውና።

ታዲያ ይህን የተገነዘቡት የአፍሪካ ሀገራት ታሪክን እንደ ሐውልት አንድ ቦታ ገትሮ ለማቆም ያሰበውን የፖለቲካል ኢኮኖሚ ፍልስፍና ወደ ጎን በማለትና ኒዮ-ሊበራሊዝም ተቋማት በየጊዜው የሚደርስባቸውን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖዎችን በመቋቋም ከራሳቸው ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም መንገድን መርጠው በመጓዝ ላይ ይገኛሉ። በዚህም ከኒዮ-ሊበራሊዝም ውጭ ማደግ እንደሚቻል ለራሳቸው ለርዕዮቱ አቀንቃኞች ሳይቀር በገሃድ እያሳዩ ናቸው። ይሁንና በሰበብ አስባቡ 'ከእኛ አስተሳሰብ ውጭ ለምን ታድጋላችሁ' የሚለው የኒዮ-ሊበራሊዝም ጫና ዛሬም ድረስ አልቀረም። እናም የርዕዮተ-ዓለሙ ደጋፊ ተቋማትና አቀንቃኞች ለታዳጊ ሀገራት አንዳች ዓይነት ድጋፍ ሊያደርጉ ሲፈልጉ በራሱ ሀገር ሳይቀር ከስሮ ዕርቃኑን የቀረውን ርዕዩት (ዓለም አቀፉን የፋይናንስ ቀውስ ያስታውሷል!) ገቢራዊ እንዲያደርጉ በግልፅ ይጠየቃሉ። ከእነዚህ ሀገራት ውስጥ ደግሞ ሀገራችን አንዷ መሆኗ የአደባባይ ምስጢር ነው።

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ነዳጅ ባይኖራትም፤ በዓለም ላይ ምጣኔ ሃብታቸው በፍጥነት በማደግ ላይ ካሉት ቻይና እና ህንድ ቀጥላ በሶስተኛነት ደረጃ የምትጠቀስ ሀገር ሆናለች– ባለፉት አስር ተከታታይ ዓመታት በአማካይ 11 በመቶ ምጣኔ ሃብታዊ ዕድገትን በማስመዝገብ። ይሁንና እንደ የዓለም ባንክ የመሳሰሉ የኒዮ-ሊበራል የፋይናንስ ተቋማትና የኒዮ-ሊበራል አቀንቃኞች ሀገራችን በፈጣንና ተከታታይ ዕድገት ውስጥ እንደሆነች ባይክዱም ቅሉ፤ የዕድገቱን ቁጥር ሆን ብለው በማሳነስ ዕድገቷ እንደነበረው እንዲቀጥል አንዳንዴ ምክር ቢጤ ነገር ለመስጠት ሌላ ጊዜ ደግሞ ልክ እንደ አሁኑ "ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ" ዓይነት ሪፖርት በማውጣት ሁኔታውን ለማጣመም ይሞክራሉ።

ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት የዓለም ባንክ “ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ” ዓይነት ሪፖርት መንግስት እንደ ፋይናንስ ተቋማት፣ ቴሌኮሙኒኬሽን፣ ሚዲያ፣ ትራንስፖርት…ወዘተ. የመሳሰሉ ትላልቅ ተቋማትን ከእጁ አውጥቶ ወደ ግል ይዞታነት እንዲያዛውራቸው ካደረገ የሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት ይበልጥ እንደሚያድግ የሚያሳስብ ነው። ታዲያ ይህ አባባል በቀጥታ የሚያመላክተው ነገር ቢኖር፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የኒዮ-ሊበራሊዝም ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ፍልስፍና እሳልተተገበረ ድረስ ምጣኔ ሃብቱ ይበልጥ አያድግም የሚል ነው። እርግጥ ሁላችንም እንደምንገነዘበው የኒዮ-ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ዋነኛ መሰረቱ ‘ሁሉም ነገር ለገበያና ለግሉ ባለሃብት መተው አለበት፤ መንግስት ህግና ሥርዓትን ከማስፈን ውጪ በምጣኔ-ሃብቱ ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም” የሚል አክራሪ አመለካከት ነው፡፡ ኒዮ-ሊበራሊዝም በየትኛውም ሀገር ውስጥ እንዲኖር የሚፈልገው የመንግስት ዓይነት ኃይል የሌለውና የቀጨጨ ስርዓትን የመምራት ኃላፊነት ብቻ ያለው እንዲሆን ነው። መንግስት ከልማታዊ ስራዎች ርቆ ጥቂት ባለሀብቶች በሀገር ኢኮኖሚ ላይ እንዳሻቸው እያዘዙ ቀሪው የህብረተሰብ ክፍል የበይ ተመልካች እንዲሆንም የፍልስፍናው ህልዮት ይሻል። መንግስት በገዛ ሀገሩ ኢኮኖሚ ውስጥ የዘበኝነት ተግባር ብቻ መወጣት አለበት ብሎም በጥብቅ ያምናል። ለዚህም ነው ለሀገራችን ጅምር ኢኖሚያዊ ዕድገት የራሳቸውን ሚና ሊወጡ የሚችሉትንና ቀደም ሲል የጠቀስኳቸውን ትላልቅ ተቋማት ለውጭ ባለሃብቶች እንዲሸጡ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሚወተውቱት።

ዳሩ ግን በእኔ እምነት ሀገራችን ይህን የኒዮ-ሊበራሊዝምን አስተሳሰብ በአሁኑ ወቅት በሶስት ምክንያቶች እንዳለ መቀበል አይቻላትም። አንደኛው በልካችን ያልተሰፋውን የኒዮ-ሊበራሎችን ጥብቆ እናጥልቀው ብንል ወይ ሊሰፋን አሊያም ሊጠበን የሚችል መሆኑ ሲሆን፤ ሁለተኛው ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ በግሉ ባለሃብት የማይከናወኑ አያሌ ተግባራት መኖራቸው ነው። ሶስተኛው ደግሞ ‘ሀገራት ከእኛ አስተሳሰብ ውጪ ሊያድጉ አይችሉም ወይም ቢያድጉም ችግር ይገጥማቸዋል’ ብሎ የሚያስበው “ሽማግሌው ርዕዮተ-ዓለም” በተፈጠረበት በእነ ሮናልድ ሬጋን ሀገር እንኳን ሳይቀር የተወገዘና እሳቤው እየተንገራገጨ በመሆኑ ጠቀሜታ ያን ያህል ስለሆነ ነው። ያም ሆነ ይህ ግን የሀገራችን መንግስትና ህዝብ ለምን ትላልቅ ተቋሞቻቸውን እንደማይሸጡ ለመገንዘብ እንችል ዘንድ ሶስቱንም ሃቆች ጠለቅ ብለን መመልከት ተገቢ ይመስለኛል።

አዎ! የኒዮ-ሊበራል ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ርዕዮተ-ዓለማዊ ጥብቆ እኛ አሁን ካለንበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር ፈፅሞ አብሮ አይሄድም። እንደሚታወቀው ኒዮ-ሊበራሊዝም በአፍሪካ ውስጥም ይሁን በሌሎች አህጉራት ውስጥ ባሉ ሀገሮች በራሱ አምሳያ ጠፍጥፎ የሰራቸው ዴሞክራሲዎች በኪራይ ሰብሳቢነት ሽሚያ ዙሪያ ከመናቆር በስተቀር በማናቸውም ጉዳዩች ላይ ጥልቅ የሆነ ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር የተሳናቸው ናቸው። በአንፃሩ ደግሞ በሀገራችን ውስጥ ገቢራዊ እየሆነ ያለው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ፈጣንና ተከታታይ ልማትን ያረጋገጠ፣ ለወደፊቱም ይበልጥ ሊያረጋግጥ የሚችል ነው። በዚህም ብሔራዊ መግባባትን መፍጠር የጀመረና በቀጣይም በተጠናከረ ሁኔታ የሚጠናከርበትን አቅጣጫ ተከትሎ በመጓዝ ላይ የሚገኝ ስርዓት በመገንባት ላይ ነው። እናም በእኔ እምነት ከዚህ አኳያ የኒዮ-ሊበራል እጀ ጠባብ ጥብቆ ሊጠበን ይችላል። ከዴሞክራሲ አኳያም ቢሆን ምንም እንኳን የሀገራችን ዴሞክራሲ ከኒዮ-ሊበራሊዝም ተፅዕኖ ነፃ ባይሆንም፤ የራሱን ፈርጅ ተከትሎ በመጓዝ ላይ የሚገኝ ነው። እንደሚታወቀው ሊበራሊዝም መቼም ቢሆን ስለ ግል እንጂ ስለ ጋራ መብት ተከራክሮ አያውቅም። በዚህም እርሱን ተከትሎ የመጣው ኒዮ- ሊበራሊዝምም የግል መብትን ትርክት ጫፍ ላይ አድርሶታል።

ይህም ርዕዮቱና አራማጆቹ በየአደባባዩ የሚያንፀባረቁት ምልከታ የግል መብት ላይ ብቻ ያነጣጠረ እንዲሆን አድርጎታል። ለአብነት ያህልም ርዕዩቱን ከሮናልድ ሬጋን ጋር በመሆን ያወጁት የቀድሞዋ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ማርጋሬት ታቸር በአንድ ወቅት “ህዝብ ብሎ ነገር የለም፣ ሁሉም ነገር በግለሰቦች ላይ የተመሰረተና የታጠረ ነው” በማለት የተናገሩትን አባባል መጥቀስ ይቻላል። ይህም ኒዮ-ሊበራሊዝም በግልና በቡድን መብቶች መካከል ያሉትና የማይለያዩ መስተጋብሮችን እንደማይቀበል የሚያመላክት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን፣ በአንድ ሀገር ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ማህበራዊ ክፍሎች የቡድን መብቶቻቸው ካልተከበረ በግልም ነፃ ሊሆኑ አይችሉም።

ይህን አባባሌን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ያህል በምሳሌነት የሴቶችን የፆታ ነፃነት ትግል ላንሳ። ሴቶች የግል መብቶቻቸው ተከብረውላቸው የሚደርስባቸው ፆታዊ አድልኦ በእኩልነት ካልተተካላቸው መቼም ቢሆን በግላቸው ነፃ ሊሆኑ አይችሉም። እናም የፆታ እኩልነት መብቶቻቸውን ማስከበር የሚችሉት በግል ሳይሆን በቡድን መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። በተለይም ጉዳዩን ከ75 በላይ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች እንዲሁም የዘመናት የመብት ጥያቄዎቻቸውን ለመመለስ የታገሉ ህዝቦች ባሉበት በእኛ

ሀገር ውስጥ መብቶች ሊከበሩ የሚችሉት በግልና በተናጠል አይደለም–በጋራና በቡድን እንጂ።

ታዲያ እዚህ ላይ ውድ አንባቢዎቼ ሀገራችን ውስጥ የግል መብት አይከበርም እያልኩ እንዳልሆነ እንደምትገነዘቡልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። እያልኩ ያለሁት የቡድንና የግል መብቶች የየራሳቸው ነፃ ህልውና ያላቸው እንዲሁም አንዱ ያለ ሌላው ሊፈፀም የማይችል መሆኑን ነው። ይህም የኒዮ-ሊበራሊዝምን እሳቤ እንዳለ ሳናላምጥ ብንውጠው ሊያንቀን አሊያም እሽ ብሎ ወደ ጉሮሮአችን ላይገባ እንደሚችል አመላካች ነው። እርግጥ ኒዮ-ሊበራሊዝም “ሁሉም ነገር ለገበያውና ለባለ ሃብቱ መተው አለበት” የሚል የገበያ አክራሪነትን የሚከተል በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግሰትና ህዝብ ቀደም ሲል በዓለም ባንክ የተጠቀሱትን ታላላቅ ተቋማቸውን እንዲሸጡ ሪፖርትን በመሳሰሉ የተለያዩ አስባቦች መጠየቁ የሚገርም አይደለም። ምክንያቱም ርዕዮቱ ሁሉንም ነገር ከራሱ ቀኖና አኳያ ስለሚመለከት ነው። ይሁንና እዚህ ላይ “ወፍ እንዳገሩ ይጮሃል” የሚለው ይትብሃል መዘንጋት ያለበት አይመስለኝም። ሁሉም ነገር አንፃራዊ ነው። አንድ ሀገር ውስጥ ያለ ዕውነታ የግድ በሌላኛው ሀገር ውስጥ ሊሰራ አይችልም። ይስራ ተብሎ የግድ ቅቡል ቢሆንም ትርፉ “መላላጥ” ከመሆን አይዘልም።

እኔ እስከሚገባኝ ድረስ እንኳንስ ‘አይሆኔነቱን’ እንደ አሮጌ ባቡር ትንሽ እንቅፋት በነካው ቁጥር በመንገራገጭ ያሳየን ርዕዮት (አሁንም እዚህ ላይ ዓለም አቀፉን የፋይናንስ ቀውስ ያስታውሷል!) ቀርቶ፣ ለሁሉም ሀገሮች የሚጠቅም እሳቤ ቢሆንም እንኳን አሁን ባለንበት ጅምር የዕድገት እመርታ ወቅት ለእኛ የሚሆነን አይደለም። አይበጀንም። እናም የዓለም ባንክና ሌሎች የኒዮ-ሊበራሊዝም ተቋማት ልማታዊው መንግስትና ህዝቡ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ትላልቅ ተቋሞቻቸውን የማይሸጡበትን ምክንያት በጥሞና ቢረዱት በጄ ነው እላለሁ–ጠንቅቀው የሚያውቁት ቢሆንም። በመሆኑም እንደ እኛ ያለ በማደግ ላይ የሚገኝ ህዝብ በዋነኛነት ምጣኔ ሃብቱን አሳድጎ “የነገ ሰውነቱን” ዕውን ለማድረግ በቀዳሚነት መጠቀም ያለበት የራሱን ገንዘብ፣ ዕውቀትና ጉልበት ነው። ሙሉ በሙሉ በውጭ መዋዕለ ንዋይ ጥገኛ መሆን የለበትም። ምጣኔ ሃብቱ በዋነኛነት ሀገር በቀል መሆን አለበት።

ከዚህ አኳያ የሀገራችን ኢኮኖሚ አሁን ባለበት ደረጃ ስናየው ገና ታዳጊና ለጋ ሆኖ እናገኘዋለን። ምንም እንኳን የግሉ ባለሃብት ለኢኮኖሚያችን ማደግ ተገቢውን ሚና እየተወጣ ቢሆንም፤ በአሁኑ ወቅት ያለው አቅም ግን ይህን ያህል ዳብሯል የሚባልበት

ደረጃ የደረሰ አይደለም። ጅምር ዕድገት ያለበት ሀገር ባለሃብት በመሆኑም አቅሙ ወደፊት እያደገና እየጎለበተ የሚሄድ ነው። እናም ይህ ባለሃብት በግሉ ዘርፍ ማከናወን ያልቻላቸውን ጉዳዮች የገበያ ክፍተት እንዳይፈጠር ልማታዊው መንግስት በተመረጠ አኳኋን ጣልቃ በመግባት ያስተካክለዋል። ይህም የገበያውን ጉድለት በመሙላት ረገድ እጅግ የላቀ ሚና ይጫወታል። እናም በልማት ሂደቱ ውስጥ የመንግስት ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ የሚሆንበት አንደኛው ምክንያት በገበያ ጉድለቱ የተከሰቱ ክፍተቶችን በማስወገድ ልማትን ለማፋጠን እንዲቻል መሆኑን መገንዘብ ይገባል። አሁን ባለንበት ሁኔታ አንድ የሀገራችን ባለሃብት ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነው ህዝብ በሚገኝበት ገጠር ወስጥ ገብቶ ትምህርት ቤቶችን፣ ክሊኒኮችን፣ መሰረተ-ልማቶችን...ወዘተ. ገንብቶ ለህዝቡ ሊሰጥ አይችልም—በተለያዩ ግላዊና ስነ-ልቦናዊ ምክንያቶች። የእነዚህ ተግባራት አለመከወን ደግሞ ለመንግስት ከገበያ ጉድለት ባለፈ የህልውና ጉዳዮች ናቸው—ልማት የሀገራችን ህዝብና መንግስት የሞት ሽረት ጉዳይ ነውና። እነዚህን ልማታዊ ተግባራት ለመከወን መንግስት ገንዘብ ያስፈልገዋል። በመሆኑም ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው ታላላቅ ተቋማት በገንዘብ ምንጭነት የግድ በመንግስትና በህዝብ እጅ መኖር አለባቸው። ከእነርሱ የሚገኘው ገንዘብም አብዛኛውን የሀገሪቱን ህዝብ ወደ አዲስ የልማት ጎዳና እንዲያመራ ያደርጋል፤ እያደረገም ነው።

ስለሆነም እኛ እንደ ኒዮ-ሊበራሎቹ የገበያ ክፍተቱን በሙሉ በግሉ ባለ ሃብት እንዲሸፈን ማድረግ ስለማንችል አቅማችን ይበልጥ እስኪጎለብት ድረስ ተቋማቱ የግድ በመንግስትና በህዝብ እጅ መቆየት ይኖርባቸዋል—ለዘመናት ተጭኖን የነበረውን የድህነት ቀንበር አሽቀንጥረን በመጣል ለምናደርገው የህዳሴ ጉዟችን መደላድል የበኩላቸውን እገዛ እያደረጉልን ናቸውና። ይህ አካሄድ ደግሞ ልማታዊውና ዴሞክራሲያዊው መንግሰት በነደፋቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እየተመራ ላለፉት አስር ዓመታት ህዝቡን በነቂስ በማሳተፍ ድህነትን ታሪክ ማድረግ እንደሚቻል በተግባር ማረጋገጡን ራሳቸው ኒዮ-ሊበራሎቹም ቢሆኑ የሚክዱት አይመስለኝም።...እንዲያውም ይህንና ይህን በመሳሰሉ የልማት አቅጣጫዎች ሀገራችን ከሰሃራ በታች ካሉ ነዳጅ የሌላቸው ሀገራት የዕድገት ሞዴል መሆኗን እነርሱው ራሳቸው ህያው ምስክር ናቸው። ታዲያ ሃቁ ይህ ከሆነ ዘንዳ፤ እዚህ ላይ 'እነ ዓለም ባንክ ምን አድርጉን እያሉ ነው?፣ መንግስት በያዘነው ልማታዊ አቅጣጫ ተጉዞ ውጤት እያመጣ እያዩና ራሳቸውም እማኝነታቸውን እየሰጡ ስለምን

የዕድገቱ አንቀሳቃሽ ሞተር የሆኑ ታላላቅ ተቋማት እንዲሸጡ ይወተውታሉ?' የሚል ጥያቄዎችን ማንሳት ያስፈልጋል።

ታዲያ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ይሆን ዘንድ የኒዮ-ሊበራሊዝምን የኋላ ታሪክ በጨረፍታም ቢሆን መመልከት ተገቢ ይመስለኛል።...ሁላችንም እንደምንገነዘበው የኒዮ-ሊበራሊዝም ፖለቲካል-ኢኮኖሚ ስርዓት በቅኝ ግዛት ዘመን የአፍሪካንና የሌሎች ድሃ አህጉራትን ሃብትና ንብረት በመመንተፍ ደልቦ ዛሬ ላይ የደረሰ ነው፡፡ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ኒዮ-ሊበራሊዝም ለአፍሪካም ይሁን ለአባል ሀገሮቿ ማደግ አይቆረቆርም። እንዲያውም ለውድቀታቸው መንስኤ ነው ብል ከዕውነታው ብዙም የምርቅ አይመስለኝም–ከአመለካከታቸው፣ ከባህላቸውና ከተፈጥሮአዊ ማንነታቸው ያፈነገጡ እሴቶችን ላያቸው ላይ በግድ ሲጭን የኖረ ርዕዮት ስለሆነ። ዳሩ ግን ርዕዮቱ ዛሬም ቢሆን ባከናወናቸው ቀደምት ተግባራቱ አልተፀፀተም። ይልቁንም ልክ እንደ ቅኝ ግዛቱ ዘመን ዛሬም በእነዚያ ድሃ ሀገራት አንጡራ ሃብት አዛዥና ናዛዥ በመሆን ተጠቃሚ ሊሆን ይፈልጋል። ስርዓቱ ሁሉንም ነገር ለባለ ሐብቱና ለገበያው የሚሰጥ መረን የለቀቀ ፍልስፍናን የሚከተል በመሆኑም፤ የድሃ ሀገራት ትላልቅ ተቋማት ሲሸጡ መግዛት የሚችሉትን ባለ ሃብቶቹን በማሰማራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ይዋትታል። እናም የውተወታው አልፋና ኦሜጋ ምኞት ይኸው ይመስለኛል።

እርግጥ ርዕዮቱ ሚሊዮን ድሆችንና ጥቂት ቱጃሮችን በመፍጠር በርካታ ድሃ ሀገራትን በፍልስፍናው ማዕበል እንደዋጣቸው እናስታውሳለን፡፡ ሚሊዮኖችን በማዕበሉ አስጥሞ ጥቂቶችን ባለፀጋ ማድረጉንም እንዲሁ፡፡ ግና ዛሬ በዘመናችን ርዕዮተ- ዓለሙ የማይፈለግ ብቻ ሳይሆን የሚያበላላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እናም አፍሪካዊያን ኒዮ-ሊበራሊዝምን በመቃወም የራሳቸውንና ከታሪካቸው፣ ከባህላቸውና ከነባራዊ ሁኔታቸው ጋር የሚጣጣም የኢኮኖሚ ሥርዓት ለመዘርጋት ተገደዋል፡፡ ውጤታማም እየሆኑ ነው፡፡ የኒዮ-ሊበራል ተቋማትንና አቀንቃኞቹን የሚያስቆጣቸው እንዲሁም በየወቅቱ በሰበብ አስባቡ የሚያነጫንጫቸው፤ ይኸው የአሮጌው አስተሳሰብ ከገበያው እየወጣ መሄዱ እንዲሁም የአፍሪካዊያንና የኤስያዊያን አዲሱ ልማታዊ አስተሳሰብ ፍሬያማ እየሆነ መምጣቱ ነው፡፡

እናም በእኔ እምነት የኒዮ-ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ቀደም ሲል አፍሪካ ውስጥ ተሞክሮ በመክሸፉ ዛሬ ላይ ጊዜው አልፎበታል–ልክ እንደ ጠለቀች ፀሐይ። አዎ! አፍሪካዊቷ ፀሐይ የጠለቀችበት እሳቤ ነው። ከአፍሪካም በዘለለ በርዕዮቱ ጠንሳሽ ሀገራት ውስጥ ሳይቀር

ክስረትን ያስተናገደ ነው። እርግጥ የኒዮ- ሊበራሊዝም ፖለቲካዊ አስተሳሰብ በተከታዩቹ ሀገራት ህዝቦች ጭምርም ሲወገዝ አድምጠናል፤ በቴሌቪዥን መስኮቶችም ከትዝብት ጋር ተመልክተናል፡፡ ርዕዮቱ በባህሪው በጥቂት የግል ባለሃብቶች ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ማህበራዊ መሰረቱ ይኸው የህብረተሰብ ክፍል ነው፡፡ እናም እጅግ የሚበዛው የህብረተሰብ ክፍልን የዘነጋው ይህ ህልዮት፤ መንግስታዊ መሰረቱ ጥቂት ባለሃብቶች ስለሆኑ ዴሞክራሲውም ለእነርሱ የቆመ ነው። በእነርሱው የሚዘወር ጭምር።

ሩቅ ሳንሄድ የቅርብ ጊዜውን ትውስታ ብቻ ብናነሳ እንኳን፤ በፋይናንስ ቀውሱ ወቅት የአሜሪካ ህዝቦች "የፍትሐዊነት ያለህ!" የሚል ጩኸትን በእማኝነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በወቅቱ "ዎል ስትሪት" የተባለውን የገበያ ማዕከል የወረሩት የዚያች ሀገር ዜጎች "እኛ 99 በመቶ የሆነውን መካከለኛ የህብረተሰብ ክፍልን ከአንድ በመቶ ባለፀጋዎች ለመታደግ ነው ሰልፍ የወጣነው" የሚል መፈክርን በወቅቱ በቴሌቪዥን መስኮት የተመለከተ ማንኛውም ሰው፤ እርግጥም የኒዮ-ሊበራሊዝም ርዕዮተ- ዓለም ፍልስፍና ፍትሐዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ማስፈን ተስኖት ህዝቦችን ምን ያህል ዋጋ እያስከፈላቸው መሆኑን ለመገንዘብ ብዙም ምርምር አይጠይቀውም፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ይህን መሰሉ "በፍትሐዊነት ተጠቃሚ መሆን አልቻልንም" የሚል ጥያቄ ያልተነሳባቸው ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ያላቸው ሀገራት፤ ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የሚከተሉት ርዕዮተ-ዓለም ትክክለኛ መሆኑን የኒዮ-ሊበራሊዝሙ አስተሳሰብ ክስረት ህያው ማረጋገጫ ሆኗል ማለት የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ቀደም ባሉት ዓመታት የርዕዮተ -ዓለሙ መሰረት የሆኑትና በጥቂት ባለሃብቶች እጅ የሚገኙት ባንኮች እና ኮርፖሬሽኖች በፈጠሩት ምጣኔ-ሃብታዊ ጣጣ ሳቢያ፤ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ቀውስ እንዲፈጠር አድርገዋል። ሆኖም መንግስታቱ አብዛኛውን ህዝብ ከቀውሱ ከማውጣት ይልቅ፣ አነዚህን ድርጅቶች በመደጎም በጣት የሚቆጠሩ ባለሃብቶችን ከኪሳራ ለማዳን ተሯሩጠዋል፡፡ ታዲያ ይህ ድርጊታቸው በየሀገራቱ ውስጥ ከስራ መቀነስንና ስራ አጦችን መፍጠርን እንዲሁም "ማህበራዊ ፍትህ ተጓደለብኝ" በሚለው ዜጋ ላይ የታክስ ጭማሪ ማስከተልን፣ በጡረታ ያለመታቀፍን እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ ቀውሶችን በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ላይ ፈጥሯል፡፡

"ጥቂት ባለሃብቶችን ታክስ አስከፍሉ፣ የስራ ዕድል ፍጠሩልን፣ ከስርዓቱ መካከለኛ ገቢ ያለው ዜጋ በሐብት ክፍፍሉ ፍትሐዊነት ተጠቃሚ መሆን አልቻለም…ወዘተ." የሚሉ

ድምፆች ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ እንዲሰሙም አድርጓል። ይህም ኒዮ-ሊበራሊዝም እንኳንስ ለሌሎች ሀገሮች ሊጠቅም ቀርቶ፣ በሀገሩ ውስጥም ተቀባይነት ማጣቱ በግላጭ እንድናየው ያደረገን እውነታ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ታዲያ ይህ ዕውነታ "ከኒዮ-ሊበራሊዝም ውጪ ሌላ አማራጭም አለ" ያሉ ሀገራትን ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታቸው ጋር የሚጣጣም ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት እንደሚችሉና በያዙት መስመር ከቀጠሉም ከኢኮኖሚያዊ ዕድገት ግስጋሴያቸው ሊስተጓጎል እንደማይችል አረጋግጧል። አዎ! ከኒዮ-ሊበራሊዝም ውጪ ማደግና መበልፀግ እንደሚቻል በአንድ በኩል ሀገራቱ በመከተል ላይ የሚገኙት ልማታዊ አካሄድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የኒዮ-ሊበራል ክስረት ተጨባጭ ምስክሮች ሆነዋል። ከተግባር የበለጠ ሃቅ የለምና በዚህ ረገድ በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ አሰራራቸው ዕድገታቸውን እያስወነጨፉ ያሉትን ኢትዮጵያን ጨምሮ እነ "ብሪክስ"ን (BRICS-ብራዚል፣ ሩሲያ፣ ህንድ፣ ቻይና እና ደቡብ አፍሪካ) በምሳሌትነት ልንጠቅሳቸው እንችላለን፡፡…በመሆኑም ሀገራችን ከህዝባቿ ታዳጊ ልማታዊ ማንነት ጋር የሚጣጣም የዕድገት ፕሮግራም በመምረጧ፣ መርጣም የስኬት ጉዞዎችን በመራመዷ ሳቢያ ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ ጋር እጅግ በሚጣረስ መልኩ 'ታላላቅ ተቋሞችሽን ሽጪና የወጪ ንግድሽን አሳድጊ' የሚል የኒዮ-ሊበራሊዝምን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ሪፖርት ማውጣት ተገቢ አይመስለኝም። ለዚህም ነው የዓለም ባንክን ርዕዮተ-ዓለም ሪፖርት "ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ ነው" የምለው። እናም ይህ የባንኩ "ከፈረሱ የቀደመ ጋሪ" ሪፖርት ከደጋፊነቱ ይልቅ እንቅፋትነቱ ይበዛልና በማንኛውም መስፈርት ቅቡል ሊሆን አይችልም። በመሆኑም ባንኩ ራሱ እየመሰከረ ያለውን ጅምር፣ ነገር ግን ፈጣን የዕድገት ዕመርታን "ይበል" ማለት እንጂ በርዕዮተ-ዓለም ፍልስፍና ጣጣ ታጥሮ አሜኬላ እሾህ ሆኖ ማደናቀፍ ያለበት አይመስለኝም። ቸር ያሰንብተን።